የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26[h] Year No 28
ADDIS ABABA 25[th] March ,2020

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፯/፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ....................................................ገጽ ፲፪ሺ፫፻፶፱

**Content**

**Proclamation No.1177/2020**

Firearm Administration and Control Proclamation ……………………………………………….Page 12359

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፯/፪ሺ፲፪**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ**

የጦር መሳሪያ ቁጥጥር የሀገርንና የህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ እንዲሁም የዜጎችን እና የህዝቦችን መብትና ደህንነት ለማስከበር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

ግለሰቦች የታጠቋቸውን የጦር መሳሪያዎች የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ተግባር ሊውሉ የሚችሉበትን እድል መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በስራ ላይ ባሉ ህጎችና አሰራሮች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ህግ መደንገግ እና ወጥነት ያለው ስርአት መፍጠር በማስፈለጉ፣

ሀገራችን ያፀደቀቻቸውን ህገወጥ የጦር መሳሪያ ቁጥጥርን የሚመለከቱ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈፀምና አለማቀፍ ትብብር ለማድረግ የሚያስችል ስርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

**PROCLAMATION No.1177/2020**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR FIREARM ADMINISTRATION AND CONTROL OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**RECOGNIZING,** that firearm control is necessary to maintain peace and security of the country and the public and is necessary to ensure rights and security of citizens and people;

**WHEREAS,** it has been found necessary to make firearms in the hands of individuals could be utilized to maintain the peace and security of the community;

**WHERE As**, it has become necessary to determine in a detailed legislation gaps not covered by existing laws and practices and create consistent system;

**WHERE AS,** it has been found necessary, to enforce international agreements concerning illicit firearm control ratified by our country and to lay down system in order to conduct international cooperation;



www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሰት አንቀጽ ፶፩(፳፩) ስለ ጦር መሳሪያ አያያዝ የፌደራል መንግስት ህግ እንደሚያወጣ የተደነገገ መሆኑን በመገንዘብ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሰት አንቀጽ ፶፭ (፪) (ሸ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፯/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ተቆጣጣሪ ተቋም" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወይም ውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ኮሚሽን ነው።

፪/ "የጦር መሳሪያ" ማለት በአስነሺ ኃይል የሚፈነዳ ወይም በፍንዳታ ኃይል ጥይትን፣ አረርን፣ቦምብን፣ ፈንጂን፣ሚሳይልን፣ ሮኬትን እና ማናቸውም ተተኳሽ ነገር በማስፈንጠር በሕይወት፣ በአካል ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሳሪያ ሲሆን ጥይትን እና ተያያዥነት ያላቸውን አባሪዎችን ይጨምራል።

፫/"ጥይት" ማለት አስነሽ፣ ቀለህ፣ እርሳስ፣ ባሩድ የያዘ ሆኖ በጦር መሳሪያ አማካኝነት የሚተኮስ ማለት ነው።

፬/"አነስተኛ የጦር መሳሪያ" ማለት በግለሰብ ደረጃ ሊያዝ የሚችል ማንኛውም አይነት ሽጉጥ ነው።

፭/"ቀላል የጦር መሳሪያ" ማለት በነፍስ ወከፍ ደረጃ የሚያዝ አውቶማቲክ፣ ግማሽ አውቶማቲክ ወይም አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ ነው።

**WHERE AS,** recognizing that, under Article 51(21) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is stipulated that the federal government enacts law on the possession and bearing of arms;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(2)(h) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Firearm Administration and Control Proclamation No. 1177/2020."

### 2.Definition

Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

1/ "Supervising Institution" means the Ethiopian Federal Police Commission or Regional Police Commission to whom the power is delegated .

2/"Firearm" means a weapon that expel a shot, bullet, bomb, missile, Rocket and any projectile by the action of an explosive which causes damage on life, body and property and it includes bullet and related materials.

3/ "Ammunition" includes cartridge cases, primers, propellant powder, bullets or projectiles that are fired by firearm.

4/ "Small firearms" means any kind of Pistol that can be used at personal level;

5/ "Light Firearms" means a firearm which is not automatic, semi-automatic, or which is not automatic that can be used personally.

www.chilot.me

፮/ "አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ" ማለት አንድ አፈሙዝ ኖሮት ምላጩ ሲሳብ የሚተኩስና አንድ ጊዜ ሲተኮስ በራሱ ጊዜ ማቀባበል የማይችል መሳሪያ ነው።

፯/"ከፊል አውቶማቲክ የጦር መሳሪያ" ማለት አንድ አፈሙዝ ኖሮት ምላጩ ሲሳብ የሚተኩስና አንድ ጊዜ ሲተኩስ በራሱ ጊዜ ማቀባበል የሚችል ነው።

፰/"ሙሉ አውቶማቲክ ጠመንጃ" ማለት ከአንድ በላይ አፈሙዝ ኖሮት ምላጩ ሲሳብ የሚተኩስ እና አንድ ጊዜ ሲተኮስ በራሱ ማቀባበል የሚችል ነው።

፱/ "ተያያዥነት ያለው እቃ" ማለት የጦር መሳሪያ መያዣ ወይም ማንገቻን ጨምሮ የማንኛውም የጦር መሳሪያ አካል፣ ክፍል፣ መለዋወጫ፣ የጥይት መያዣ መጋዘን፣ እና የጦር መሳሪያውን ለማፅዳትና ለመጠገን የሚያገለግሉ እቃዎችን ይጨምራል።

፲/"ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ የጦር መሣሪያ ነው።

፲፩/"ብዛት ያለው ጉዳት አድራሽ ዕቃ" ማለት ሦስትና ከዚያ በላይ የሆነ ተመሳሳይነት ያለው ለጉዳት አድራሽ ዕቃ ነው።

፲፪/"የውግ ቁጥር" ማለት የጦር መሳሪያውን ያመረተው ፋብሪካ ቁጥርና ፊደላትን በመጠቀም የተመረተበትን ሀገር እና መለያ ቁጥር የሚያመለክት ከጥይት ካዝናው በስተቀር በሁሉም የጦር መሳሪያው አካላት ላይ በቀላሉ ለመልቀቅ በማይችል መልኩ አንድን የጦር መሳሪያ ከሌላ የጦር መሳሪያ ለመለየት የሚያስችል ልዩ ምልክት ነው።

፲፫/"ጉዳት አድራሽ ዕቃዎች" ማለት በስለታማነታቸው ምክንያት ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል በመጠቀም ወይም መርዛማ በመሆናቸው በሰው አካልና ህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለማድረስ የሚችሉ እንደ ሳንጃ፣ ገጀራ፣ሜንጫ፣ ጦር፣ ቀስት ጎራዴ፣ ሴንጢ እና መሰል መሳሪያዎችን ያጠቃልላል።

6/ "None automatic firearm" means a weapon with one barrel and can fire while it is trigger is pulled out and cannot Reload by itself when it is fired.

7/ “Semi automatic Firearm” means weapon with one barrel and which does not fire more than one shot while its trigger is pulled and can reload by itself when it is fired.

8/ “Fully automatic weapon” means weapon with more than one barrel and which could fire more than one shot while its trigger is pulled and can reload by itself when it is fired.

9/“Related material”, means firearm holder or holster, any components, parts, replacement, bullet magazine holder and materials used for firearm cleaning and repairing.

10/ "Bulk Firearm " means two or more Fire arms.

11/"Bulk Harm inflicting materials means" three or more more similar items for damage relief.

12/“Serial number” is a special mark engraved by the manufacturer using alphabets and numbers to identify country of manufacture and unique number that does not easily erase and which enables to differentiate one firearm from the other.

13/“harm inflicting materials” means weapons due to their sharpness, poison or by using electric power could inflict grave injury against life or human body like bayonet, machete, sword, dagger,mencha,spear ,centti and includes other similar materials.

www.chilot.me

፲፬/ "ፍቃድ" እና "ባለፍቃድ" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ በዚህ አዋጅ ክፍል አራት መሰረት በተቆጣጣሪ ተቋም የሚሰጥ ፍቃድ እና ፍቃዱ የተሰጠው ሰው ማለት ነው።

፲፭/"ህግ አስከባሪ" ማለት የፌደራል ወይም የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ ሚሊሻ፣ የፌደራል ወይም የክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፣ የፌደራልና የክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተቋማትና ፍትህ ቢሮዎች እና የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ናቸው።

፲፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከቱትን ክልሎች ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል።

፲፯/የተሟላ ጤንነት ሁኔታ አለመኖር" ማለት በእድሜ፣ በአእምሮ ሁኔታ ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ በህጋዊ መንገድ ያገኘውን የጦር መሳሪያ በአግባቡ ለማስተዳደርም ሆነ ለመጠቀም አለመቻል ነው።

፲፰/ "ፍርድ ቤት" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ፍርድ ቤት ነው።

፲፱/"ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፳/በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

፫.**<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፯ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በመከላከያ ሰራዊት እና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

14/ "License" and "License holder" respectively means license given by the supervising institution in accordance with part four of this Proclamation and the person who is licensed.

15/"Law Enforcement" means Federal or Regional Police Commissions, Federal or Regional Prison Commissions, Militia,Federal or Regional Attorney General Institutions and Justice Offices and Ethiopian Wild life Development and Protection Auhority.

16/"Regional State " means any of those regional states specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa Cities Administrations .

17/"Unsound health status" means unable to manage or use firearm retained through legal means because of age ,mental health condition or other reasons.

18/ "Court" means any court in Ethiopia;

19/ "Person" means any natural or juridical person;

20/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **<u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation shall be applicable up on any person within Ethiopia.

2/ Without prejudice to application of Article 27 of this Proclamation, this Proclamation shall not be applicable on Defense Forces and National Intelligence and Security Services.

www.chilot.me

## ክፍል ሁለት

## ስለ ጦር መሳሪያና አጠቃቀም ክልከላዎች

**፬. የተከለከሉ ተግባራት**

በዚህ አዋጅ መሰረት ከተፈቀደለት ሰው ውጪ ማንኛውም ሰው፡-

፩/ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ፣ የጦር ሜዳ መነፅር፣ በጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛውም አይነት መነፅር ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምፅ ለማስወገድ የሚያገለግል መሳሪያ ወደ ሀገር ማስገባት፣ ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ መገልገል፣ ማሳየት፣ መደለል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ማስተላለፍ፣ ማዘዋወር፣ ማጓጓዝ፣ ማምረት፣ ማሰልጠን፣ መጠገን ወይም ማስወገድ፣

፪/ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው ለልማት ሥራ የሚውሉትን ሳይጨምር ብዛት ያለው የጉዳት አድራሽ እቃ ወደ ሀገር ማስገባት፣ ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ ወይም ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ መደለል፣ መሸጥ ወይም መግዛት፣ ማዘዋወር፣ ማጓጓዝ፣ ማምረት፣

፫/ በአምራቹ ወይም በተቆጣጣሪ ተቋም የተሰጠ የጦር መሳሪያን የውግ ቁጥርን በሙሉ ወይም በከፊል መቀየር፣ ማጥፋት ወይም በማናቸውም አይነት ሁኔታ ተለይተው እንዳይታወቁ ማድረግ፣

፬/ የጦር መሳሪያን ወይም የጦር መሳሪያን የተመለከተ አገልግሎት ማስተዋወቅ፣

የተከለከለ ነው።

**፭. የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት የተከለከለባቸው ስፍራዎች**

፩/ማንኛውም ሰው፡-

ሀ)ሰላማዊ ሰልፍ ወይም አድማ በሚደረግባቸው ስፍራዎች፣

ለ)በምርጫ ህግ ወይም በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሚወሰኑ ስፍራዎች፣

ሐ)በሆቴሎች፣ በሲኒማና ትያትር ቤቶች፣ በሙዚየሞችና ተመሳሳይ በሆኑ የህዝብ መዝናኛ ስፍራዎች፣

## Part Two

## Firearm and Prohibition of its Use

4.**Prohibited Activities**

No one other than those given permission in accordance with this proclamation shall:-

1/ without valid license import, export, possess, put, store, use, exhibit, broker, sale, buy, transfer, traffic, transport, manufacture, train, repair or dispose firearm, military binoculars; any kind of goggles or sound muzzling instrument which may be fitted on firearm.

2/Without valid license and excluding those destined for development purposes, import, export, hold, store, use, exhibit, hoard, broker, sell or purchase, traffic, transport, manufactureharmful materials.

3/alter in whole or in part, destroy or make unrecognizable in any other way the serial number of a firearm given by the manufacturer or Supervising Institution.

4/ Advertise firearm or service related with firearm.

5. **Prohibited Places to Carry Firearm**

1/Any person shall not carry firearm in:

a) places where there is peaceful demonstration or riot,

b) places determined by Electoral Law or National Electoral Board,

c) hotels, cinema, theaters, museums and similar public recreation places,

www.chilot.me

መ)የተኩስ ስፖርት ከሚካሄድበት ውጪ በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣

ሠ)በትምህርት ተቋማት፣ በሀይማኖትና እምነት ተቋማት ግቢ ውስጥ፣ እና

ረ)በሆስፒታልና ክሊኒኮች፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና በሌሎች ተመሳሳይ ለህዝብ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ስፍራዎች፣

ሰ) በብሔራዊ ፓርኮች ወይም በዱር እንስሳት መጠለያዎች፤

ሸ) የጦር መሣሪያ ለመታጠቅ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃድ ከተሰጠው ክልል ውጪ ባሉ የክልልና ትላልቅ ከተሞች የጦር መሣሪያውን ለሕዝብ በሚታይ መልኩ ታጥቆ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ በተገለፁት ስፍራዎች ውስጥ ለመግባት የፈለገ ማንኛውም የጦር መሳሪያ የያዘ ሰው በቅድሚያ የጦር መሳሪያውን ለተቋማቱ የጥበቃ ሰራተኞች ማስረከብ ይኖርበታል፣

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም በስራ ላይ ያሉ ህግ አስከባሪዎች ወይም ተቋማቱን እንዲጠብቁ የተቀጠሩ የጥበቃ ሰራተኞች የተፈቀደላቸውን የጦር መሳሪያ በመያዝ ስራቸውን ለማከናወን ይችላሉ፣

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ከተጠቀሱት ስፍራዎች በተጨማሪ ተቆጣጣሪው ተቋም ሌሎች የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት የሚከለከልባቸው ስፍራዎች በመመሪያ መወሰን ይችላል።

**ክፍል ሶስት**

**ለጦር መሳሪያ ፈቃድ እና አስተዳደር**

**፮.የጦር መሳሪያ ፈቃድ እና የፈቃዱ ሁኔታ**

፩/ የጦር መሳሪያ ፈቃድ የሚሰጠው:-

ሀ) ለግለሰብ የሚፈቀደው የጦር መሳሪያ አይነትና ብዛት እንዲሁም የጥይት ብዛት በከተሞች አካባቢ፣ በአርብቶ አደር እና አርሶ አደር አካባቢ ያለውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ

d) sporting places except in permitted shooting sport place;

e) educational institutions, religious and belief institutions compound; and

f) Hospital and clinics, government offices and other similar places where public service is provided.

g)/ at national parks or wild life shelters.

h)a person authorized to take up a firearm is prohibited to carry a weapon in public, in large cities and Regions outside of his jurisdiction.

2/any person who is carrying a firearm and would like to enter into places mentioned under sub article /1/ of this Article shall first handover the firearm to the security guards of the institution;

3/ notwithstanding sub article 1 of this Article, law enforcement bodies on duty or security guards hired to guard the institution may carry their licensed firearm and conduct their activity;

4/ In addition to places indicated under sub article 1 of this Article, the Supervising Institute may determine by directive other places where carrying firearm is prohibited.

**PART THREE**

**FIREARM LISECENCE AND ADMINISTRATION**

6. **Condition under which Firearm License is Given**

1/ Firearm license shall be given:

a) the type and quantity of firearms and the number of ammunition allowed for an individual in urban ,pastoralist and farmers' areas, shall be determined by a directive to be issued by the Supervising Institution;

www.chilot.me

በማስገባት ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

ለ) ለድርጅት የሚፈቀደው የጦር መሳሪያ ዓይነትና ብዛት እንዲሁም የጥይት ብዛት ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

ሐ) አመልካቹ ከዚህ ቀደም ሌላ የጦር መሳሪያ ፈቃድ የሌለው ወይም ፈቃዱን መልሶ ያሰረዘ ከሆነ፣

መ) ፈቃድ የተጠየቀበት የጦር መሳሪያ ከዚህ ቀደም በሌላ ሰው ስም ፈቃድ ያልወጣበት ከሆነ፣

ሠ) የጦር መሳሪያው የሚሰራና ያልተበላሸ ከሆነ፣

ረ) የጦር መሳሪያው ወንጀል ያልተሰራበት ከሆነ፣

ሰ)የጦር መሳሪያው የውግ ቁጥር የሚታይ ከሆነ ነው። ሆኖም በዚህ አዋጅ የመሸጋገሪያ ጊዜ ወቅት ፈቃድ የተጠየቀበት የጦር መሳሪያ መለያው የማይታይ ከሆነ በተቋሙ የውግ ቁጥር ታትሞ ፈቃድ ይሰጠዋል፡

፪/ከዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩)(ሀ) በስተቀር ሌሎች የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች የህግ ሰውነት ለተሰጣቸው ድርጅቶችም ያገለግላሉ፣

፫/ በዚህ አንቀፅ መሰረት ለግለሰብ የሚሰጥ ፈቃድ ለሁለት አመት፣ ለድርጅት የሚሰጥ ፈቃድ ደግሞ ለሦስት ዓመት ፀንቶ ይቆያል።

፬/ ከላይ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በነበረው አሰራር መሰረት የተመዘገበ የጦር መሳሪያ ወይም ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ ባስመዘገበው ወይም ባለው ፍቃድ መሰረት የጦር መሳሪያው ይመዘገብለታል።

**፯.<u>የጦር መሳሪያ ፈቃድ የሚሰጥባቸው መስፈርቶች</u>**

ለግለሰብ የጦር መሳሪያ ፈቃድ የሚሰጠው ፈቃድ ጠያቂው:-

፩/የተገለፀው ጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ በተጠቀሱት

b)The type and quantity of firearms allowed for an organization, as well as the number of ammunition allowed shall be determined by a directive to be issued by the Supervising Institute;

c) if the applicant does not have another previous license or has returned the license and got canceled it;

d) the firearm is not licensed in the name of another person,

e) if the firearm is working and is not damaged;

f) if the firearm is not used for committing a of crime;

g) if the serial number is visible. However, during the transitory period of this proclamation, if the identification number is not visible the institution shall print serial number and give license;

2/except sub article 1/a/ of this article, all conditions shall also be applicable to legal persons;

3/ License given to individuals shall remain valid for two years and for legal persons for three years.

4/ Notwithstanding this proclamation, legally registered firearms and individuals licensed by the previous licensing regime will be automatically registered based on previously provided details.

7. **Requirements for Firearm Licensing**

Firearm license for individuals shall be given where the applicant:

1/ After the expiry of the period specified, if a resident in a

www.chilot.me

አካባቢዎች የሚኖር ሰው የጦር መሳሪያ ፈቃድ ሲጠይቅ የህብረተሰቡን ልዩ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈቃድ ይሰጠዋል፣

፪/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ያለው፣

፫/ የአደገኛ ዕፅ ወይም የመጠጥ ሱስ የሌለበት፣

፬/ተቆጣጣሪው ተቋም ረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውል የጦር መሳሪያ በፍቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ የሚሰበሰብበትን ስርዓት ይዘረጋል፡፡

፭/በሙሉ ወይም በከፊል በፍርድ ወይም በህግ ችሎታውን ያላጣ፣

፮/ የአእምሮው ሁኔታ የተስተካከለ እና አላስፈላጊ የሀይል አጠቃቀም ባህሪ የሌለው መሆኑ በተቆጣጣሪው ተቋም የታመነበት፣

፯/የጦር መሳሪያን አጠቃቀም እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሰረት ያለበትን ግዴታ ግንዛቤ ያለው ወይም በተቆጣጣሪው ተቋም ስልጠና እንዲወስድ ሲጠየቅ ፈቃደኛ የሚሆን፣

፰/ለጦር መሳሪያ ፈቃድና እድሳት አስፈላጊውን ክፍያ የሚከፍል፣

፱/ከሚኖርበት አካባቢ አስተዳደር መልካም ስነምግባር ያለው ለመሆኑ የትብብር ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል፣ እና

፲/ በአንቀፅ ፱(፩)እና(፪) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በተቆጣጣሪው ተቋም በሚዘጋጅ ወጥነት ያለው መስፈርት መሰረት የጦር መሳሪያ ለመያዝ በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ የታመነበት፣

ሲሆን ነው።

፲፩/ለድርጅት የጦር መሳሪያ ለመያዝ የሚያስፈልጉ መስፍርቶችን ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

## ፰. <u>በልማድ ለታጠቁ የህብረተሰብ ክፍሎች የጦር መሳሪያ ፈቃድ ስለመስጠት</u>፡-

፩/ በተለምዶ የጦር መሳሪያ የሚያዝባቸው አካባቢዎች

specified area requests a firearm license, he shall be granted a permit, taking into account the special circumstances of the community,

2/ is an Ethiopian national or has permit to reside in Ethiopia;

3/ is not drug or alcohol addict;

4/ The Supervising Authority shall establish a voluntary collection system for unused firearms because of long- lived services.

5/ has not partially or fully lost capacity as a result of legal or judicial interdiction;

6/ Believed by the Supervising Institution to have balanced mental status and does not have unnecessary aggressive nature ;

7/ has understanding of firearm utilization and the duties under this Proclamation or has willingness to take a training when requested by the Supervising Institute;

8/ is willing to pay the necessary payment for Licensing and renewal of License,

9/ could submit letter of cooperation that he has good conduct from his residential local administration; and

10/ without prejudice to Article 9 (1) and (2) is believed to have sufficient and valid reason to bear firearm based on a consistent requirement to be prepared by the Supervising Institution.

11/ The requirements for organizations to have a firearm shall be determined by a directive to be issued by the supervising Institute.

## 8. <u>Firearm Licensing of Traditionally Armed Communities</u>

1/ Individuals who carry firearm and are residents of localities where firearm is traditionally carried shall

www.chilot.me

ነዋሪ የሆኑ እና የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎች፣ ተቆጣጣሪው ተቋም በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ) በሚያወጣው መመሪያ እና በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ በአካባቢያቸው ተገኝቶ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ ሲጠይቁ የጦር መሳሪያ የህብረተሰቡን ልዩ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ አዋጅ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል።

be given a license in accordance with a directive to be issued based on sub-article (1) (a) of Article 7 this Proclamation, and within the two-year time taking into account the special circumstances of the community.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩ የተገለፀው ጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚኖር ሰው የጦር መሳሪያ ፈቃድ ሲጠይቅ የኅብረተሰቡን ልዩ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈቃድ ይሰጠዋል፣

፫/ በዚህ አንቀፅ በተገለፀው ጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃድ ያልወጣበት የጦር መሳሪያ ለተቆጣጣሪው ተቋም ገቢ መደረግ አለበት፣ በቁጥጥር በተገኘም ጊዜ ይወረሳል።

፬/ ተቆጣጣሪው ተቋም ረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውል የጦር መሣሪያ በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ የሚሰበሰብበበትን ሥርዓት ይዘረጋል።

2/After the expiry of the period specified in sub-article (1), if a person residing in the specified areas requstes for a firearm license, he shall be granted a permit, taking into account the special circumstances of the society,

3/A firearm not licensed within the time limit as indicated under this Article, shall be delivered to the Supervising Institution, when found during supervision, it shall be confiscated.

4/The Supervising Institution establishes a voluntary collection system for unused firearms due to their long history.

**፱.የአለም አቀፍ ድርጅቶችና የውጪ ሀገር ተወካዮች ስለሚሰጥ ፈቃድ**

፩/ የአለማቀፍ ድርጅቶች ወይም የውጪ ሀገር ተወካዮች የጦር መሳሪያ ለመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተያየት በተቆጣጣሪ ተቋሙ በሚወጣ መስፈርት መሰረት ይሆናል፣

፪/ ተቆጣጣሪው ተቋም ፈቃድ የሚሰጠው የጦር መሳሪያ በዚህ አዋጅ የተፈቀደው አይነት መሆኑን ያረጋግጣል፣ የጦር መሳሪያው ወደ ሀገር ሲገባ መለያውን ይመዘግባል፣ ፈቃዱ ሲያበቃም የጦር መሳሪያው ከሀገር እንዲወጣ ወይም ለተቆጣጣሪው ተቋም ገቢ እንዲሆን ያደርጋል።

**9. Firearm License for International Organizations and Foreign Representatives**

1/Firearm license shall be given to international organizations or foreign state representatives based on requirements to be laid down by the Supervising Institution with the opinion of the Ministry of Foreign Affairs;

2/ The Supervising Institution shall make sure that the firearm is of a type authorized under this proclamation; register its identification number when it is imported, and the fire arm shall be withdrawn from the country or shall be handed over to the Supervising Institution after the lapseof the license period.

www.chilot.me

**፲.የጦር መሳሪያ ፈቃድ ይዘት**

የጦር መሳሪያ ፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፡-

፩/ የባለፈቃዱን ሙሉ ስም፣ ፎቶ፣ የትውልድ ቀን፣ አሻራ፣ አድራሻ፣

፪/ የጦር መሳሪያውን አይነት፣ የውግ ቁጥር፣ የጥይት ብዛት፣ ተዛማጅ እቃ፣

፫/ ፈቃዱን የሰጠው ባለስልጣን ስም፣ ፊርማ፣ ማህተም፣ ፈቃዱ የተሰጠበት ቀን እና ፈቃዱ የሚያበቃበት ቀን።

፬/ ሌሎች በተቆጣጣሪው ተቋም በመመሪያ የሚያወጣቸውን መስፈርቶች።

**፲፩.የጦር መሳሪያ የውግ ቁጥር**

፩/ ተቆጣጣሪው ተቋም ወጥ የሆነ የውግ ቁጥር የሌላቸው የጦር መሳሪያዎች ወጥ የሆነ የውግ ቁጥር እንዲኖራቸው ያደርጋል፣ ይመዘግባል፣

፪/ተቆጣጣሪ ተቋም የውግ ቁጥር ለሌላቸው ወይም የተሰጣቸው የውግ ቁጥር ለተፋቀ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ለተቀየረ ወይም ለመለየት በማይቻል ሁኔታ ለተደመሰሰ የጦር መሳሪያዎች ፍቃድ ሊሰጥ አይችልም፣ ሆኖም በዚህ አዋጅ የመሸጋገሪያ ጊዜ ወቅት ፈቃድ የተጠየቀበት የጦር መሳሪያ የወግ ቁጥር የማይታይ ከሆነ በተቋሙ መለያ ቁጥር ታትሞ ፈቃድ ይሰጠዋል።

፫/ ለስፖርት ውድድር ፈቃድ የሚሰጠው የጦር መሳሪያ አይነትና ብዛት እንዲሁም የጥይት ብዛት ስፖርቱን ለማከናወን የሚያስችል አይነት ሆኖ ዝርዝሩ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል።

፬/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ ከተገለፀው ውጪ ማንኛውም ሰው በይዞታው ስር የሚገኝ የጦር መሳሪያ የውግ ቁጥር በማንኛውም ምክንያት ለመለየት በሚያስቸግር ሁኔታ የጠፋ ወይም የተደመሰሰ ወይም የተቀየረ እንደሆነ ወዲያውኑ ለፍቃድ ሰጪው ተቋም የውግ ቁጥር እንዲሰጠው ወይም መሳሪያውን እንዲቀይርለት ማሳወቅና

**10. Content of Firearm License**

Firearm license shall contain the following information:

1/Full name of the licensed person, photo, birth,fingerprint, date, address;

2/ Type of firearm, serial number, number of bullets, related material;

3/Name of licensing official, signature, stamp, date of license and expiry date of license.

4/ Other requirements set by the directive of the Supervising Institution.

**11. Firearm Serial Number**

1/ The Supervising Institution shall give consistent serial number to firearms which do not have consistent serial number and register them;

2/ The Supervising Institution shall not give license to firearms which do not have serial number or whose given serial number is partially or totally modified or debased beyond recognition; however, during the transitory period of this proclamation, the Institution shall print serial number and give license to firearm whose identification is illegible;

3/The type and quantity of firearms licensed for sport competition and the number of ammunition shall be adequate to carry out the sport competition .The details shall be determined by a directive to be issued by the Supervising Institution.

4/Any person where, in circumstances other than sub article 2 of this Article, the serial number of a firearm under his possession is illegible, scratched or modified shall immediately inform and handover to the Supervising Institution to have another serial number or replaced with another firearm.

www.chilot.me

ማስረከብ አለበት።

**፲፪.<u>ለልዩ ልዩ ተግባር ስለሚሰጥ የጦር መሳሪያ ፈቃድ</u>**

ለልዩ ተግባር የጦር መሳሪያ ፈቃድ የሚሰጠው:-

፩/ አመልካቹ እንደ አግባብነቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት የተጠየቀውን ተግባር ለማከናወን እንዲችል የትብብር ደብዳቤ ሲያቀርብ፣

፪/የሚያስፈልገውን የመሳሪያ አይነትና ጥይት ብዛት፣ የአገልግሎቱንና የሚጠቀምበትን ሁኔታና የአገልግሎቱ ጊዜ በዝርዝር ገልፆ ፈቃድ ሲጠይቅ፣

፫/ ለስፖርት ውድድር ፈቃድ የሚሰጠው ጦር መሣሪያ ዓይነትና ብዛት እንዲሁም የጥይት ብዛት ስፖርቱን ለማከናወን የሚያስችል ዓይነት ሆኖ ዝርዝሩ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል፣

፬/የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ተቆጣጣሪ ተቋሙ ለህጋዊ የእንስሳት አደን የጦር መሳሪያ ለመጠቀም የሚያስችል ፍቃድ ይሰጣል፣

፭/ለቲያትርና ፊልም ስራ ሲሆን የጦር መሳሪያ እንደ አግባብነቱና ፊልሙን ለመሥራት የሚያስፈልገውን የጦር መሣሪያ ሆኖ የሚፈቀደው ጥይትም በተኩስ ሀይል ተስፈንጥሮ የሚሄድ እርሳስ የሌለው ነገር ግን ሲተኮስ ድምፅ የሚያሰማ ጥይት ይሆናል፣ የጥይቱ ብዛትም ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

፮/ የጦር መሳሪያ ኤግዚቢሽን ለማሳየት እና ከተሰሩ ሀምሳ አመት ያለፋቸው የጦር መሳሪያዎችን በቅርስነት ለመያዝ በቅድሚያ የጦር መሳሪያዎቹን አይነት፣ ጥበቃ እና መሰል ጉዳዮችን ተቆጣጣሪው ተቋም በሚወስነው መሰረት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፣

፯/ በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ተቆጣጣሪው ተቋም

**12. <u>Firearm License for Special Activity</u>**

Firearm license for special activity shall be given:

1/ Where the applicant presents cooperation request letter from concerned government institutions to perform the requested activity;

2/Where license is requested with the details of the required firearm type, bullet amount, the condition of utilization, the duration of utilization;

3/ The type and amount of firearm and number of bullets for sports competitions shall be appropriate to undertake the sports events and its details shall be determined by a directive to be issued by the supervising institution.

4/ For legal animal hunting, the Supervising Institution shall give license to hunters based on the Ethiopian Wild Animal Development and Protection Authority requirements;

5/ For theatre and film works and the type of the firearm shall be considered as appropriate and necessary for the action and the bullet to be allowed shall be false bullet which does not have lead but emits sound when fired. The amount of bullets shall be determined by the directive issued by the Supervising Institution;

6/ for firearm exhibition and for preserving antique firearms which are manufactured before fifty years and the Supervising Institution may give license based on its decision on the type of firearms, their secure protection and similar matters;

7/ The Supervising Institution shall determine the validity period of license given under this article,

www.chilot.me

እንደሁኔታው ይወስናል፣ የፈቃዱ ጊዜ ሲያበቃ ባለፈቃዱ ፈቃዱ እንዲታደስለት ሲጠይቅ ሊታደስለት የሚገባ ሆኖ ከተገኘ ፈቃዱ ይታደስለታል፤ ፈቃዱ የማይታደስ ከሆነም የጦር መሳሪያው፣ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፣

፰/ ተቆጣጣሪው ተቋም ባለፈቃዱ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሌሎች ተጨማሪ ሁኔታዎችን ሊወስን ይችላል።

## ፲፫·የጦር መሳሪያ ፈቃድ ስለሚታደስበት ስርአት

፩/የጦር መሳሪያ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የፈቃዱ አገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ ከ፷ ቀናት በፊት የእድሳት ጥያቄውን ለተቆጣጣሪው ተቋም ማቅረብ አለበት፣

፪/ተቆጣጣሪው ተቋም ጥያቄው እንደቀረበለት ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው የጊዜ ገደብ መሠረት የፈቃድ መስጫ መስፈርቶቹ መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ፈቃዱን ያድሳል፣

፫/ በዚህ አንቀፅ መሰረት በቀረበ የእድሳት ማመልከቻ ላይ ተቆጣጣሪው ተቋም ውሳኔ ሳይሰጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተጠቀሰው ጊዜ ያበቃ እንደሆነ ተቆጣጣሪው ተቋም በእድሳት ጥያቄው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የቀድሞው ፈቃድ እንደፀና ይቆያል።

## ፲፬.የጦር መሳሪያ ፈቃድ ስለማገድ

፩/ማንኛውም የጦር መሳሪያ ፈቃድ ሊታገድ የሚችለው፡-

ሀ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ያቀረባቸው ማስረጃዎች አጠራጣሪ ሆነው ሲገኙና ጉዳዩን ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ) ባለፈቃዱ የጦር መሳሪያውን ላልተፈቀደለት ተግባር ስለማዋሉ ወይም ይህን አዋጅ ለመጣሱ በቂ ጥርጣሬ ሲኖር፣

ሐ)የተሰጠው ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃና ያልታደሰ ከሆነ፣

ይሆናል።

upon expiry of license period and request of the license holder ,the license may be renewed, if it is not to be renewed, it has to be delivered to the government;

8/ The Supervising Institution may determine additional conditions which need to be met by the applicant.

## 13. Firearm License Renewal System

1/ Any licensed person shall submit his renewal request to the Supervising Institution within sixty days before the expiry of the license;

2/ The Supervising Institution shall renew the license, if licensing requirements are met according to a directive and time limits issued by the Supervising Institution.

3/Where the duration indicated under sub article 1 of this Article lapses before decision is given on renewal application by the supervising institution, then the previous license shall remain valid until the Supervising Institution gives its decision on the renewal application.

## 14. Suspension of Firearm License

1/ Any firearm license shall be suspended where:

a) The evidences presented by the licensed person are found to be suspicious and it becomes necessary to investigate the case;

b) There is sufficient suspicion that the license holder has utilized the firearm for unauthorized activity or violated this proclamation;

c) After expiry of the license period without renewal.

www.chilot.me

፪/እግድ የደረሰው ማንኛውም ሰው በእግዱ ጊዜ ውስጥ የጦር መሳሪያው በተቆጣጣሪው ተቋም እጅ እንዲቆይ ያደረጋል፡፡

፫/በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው የእገዳ ምክንያቶች በ፷ ቀናት ውስጥ የጦር መሳሪያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማስተካከል ካልቻለ የጦር መሳሪያው በተቆጣጣሪ ተቋሙ ይወረሳል፡፡

## ፲፭.የጦር መሳሪያ ፈቃድ ስለመሰረዝና መውረስ

፩/ማንኛውም የጦር መሳሪያ ፈቃድ ሊሰረዝ የሚችለው፡-

ሀ) መሳሪያው ወንጀል የተፈፀመበት መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣

ለ) ባለፈቃዱ ሲሞት፣ ያለበት አድራሻ ሳይታወቅ ሲቀር ወይም በፍርድ ወይም በህግ ችሎታውን ሲያጣ፣

ሐ)ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ከፈረሰ ወይም ከተዘጋ፣

መ) ፍርድ ቤት ፈቃዱ እንዲሰረዝ ሲወስን፣

ሠ) ባለፈቃዱ በራሱ ፍላጎት ፈቃዱን ሲመልስ፣

ረ) ፈቃዱን ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች አንዱ የተጓደለ መሆኑ ሲታወቅ፣

ሰ) ባለፈቃዱ ያቀረባቸው ማስረጃዎች የተጭበረበረ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑ ሲታወቅ፣

ሸ) ባለፈቃዱ ይህን አዋጅ ተላልፎ ከተገኘ፣

ቀ) ፈቃድ የተሰጠበት የጦር መሳሪያው አገልግሎት ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ ከተበላሸና ሊጠገን የማይቻል ከሆነ፣

በ) ከዚህ አዋጅ የመሸጋገሪያ ጊዜ በኋላ የጦር መሳሪያው የውግ ቁጥሩ በማንኛውም ምክንያት የማይለይ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ተ) የጦር መሳሪያው በተለያዩ ምክንያቶች ከባለቤቱ ቁጥጥር ውጪ መሆኑ ሲታወቅ፣

ናቸው፡፡

2/ Any person whose license is suspended shall keep the firearm with the Supervising Institution;

3/ The firearm shall be confiscated by the Supervising Institution, if the licensed person could not correct the grounds of suspension stipulated under sub article 1 of this Article within sixty days.

## 15. Revocation and Confiscation of Firearm License

1/any firearm license may be revoked where:

a) it is proved by the court that Crime is Committed with the licensed persons firearm;

b) the licensed person dies, his address is unknown or becomes legally or judicially interdicted;

c) the licensed organization is liquidated or cease to exist;

d) the court orders the license to be revoked;

e) the licensed person returns the license voluntarily;

f) it is known that one of the requirements for acquiring the license is missing;

g) it is known that the information the license holder presented are forged or acquired by fraud;

h) the licensed person is found to have violated this proclamation;

i) the licensed firearm is damaged such that it is incapable to render service and is beyond repair;

j) the serial number of the firearm is unrecognizable for any reason after the transitional period of this proclamation; or

k) it is known that the firearm is out of the control of the owner for different reasons.

www.chilot.me

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት ፈቃዱ የተሰረዘ የጦር መሳሪያ ይወረሳል፣

፫/ፈቃዱ በዚህ አዋጅ መሰረት የአገልግሎትና የእድሳት ጊዜው ያበቃ እንደሆነ እና ባለፈቃዱ በቂና አሳማኝ ምክንያት ያለው መሆኑ ካልታወቀ በቀር ፈቃዱ ይሰረዛል፣ የጦር መሳሪያውም ይወረሳል።

**፲፮.ለጦር መሳሪያ ፈቃድና እድሳት የሚከፈል ክፍያ**

ተቆጣጣሪው ተቋም፡-

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት ለተፈጥሮ ሰው የጦር መሳሪያ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለማሳደስ፣

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት በህግ ሰውነት ለተሰጠው እና ለውጭ ሀገር ዜጋ የጦር መሳሪያ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለማደስ፣

፫/ ማንኛውም ፍቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃድ ጊዜው ካበቃ በኋላ በሁለት ወር የእግድ ጊዜ ውስጥ ፍቃዱን ለማሳደስ የሚከፍለውን የቅጣት መጠን፣

፬/ የጦር መሳሪያ ለልዩ ተግበር ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለማደስ፣

፭/ የጦር መሳሪያ ምልክት ለማድረግ ወይም ለማደስ፣

፮/ የተፈቀዱ የጦር መሳሪያዎችን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ፣

በደንብ በሚወሰነው መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል።

**፲፯.የጦር መሳሪያ ምዝገባ ስርአት**

ተቆጣጣሪ ተቋም በሀገሪቱ የሚገኙ የጦር መሳሪያዎችን በሙሉ በውግ ቁጥራቸው መሰረት በመረጃ ቴክኖሎጂ ስርአት መዝግቦ ያስተዳድራል።

2/ A Firearm which a license of it is revoked in accordance with sub article /1/ of this Article, shall be confiscated;

3/ The license shall be revoked and the firearm confiscated where the license and renewal period expires in accordance with this proclamation and it is not known whether the license holder has sufficient and valid reason.

**16. Firearm License and Renewal fee**

The Supervising Institution shall collect service fee to be determined by Regulation for the following services:

1/ firearm licensing or its renewal to natural person in accordance with this proclamation;

2/ firearm licensing or its renewal to legal person and foreigner in accordance with this proclamation;

3/ Renewal fine to be paid during the two months suspension period after expiry of a license of any licensed person;

4/ Licensing or renewal for special activity firearm license;

5/ To put firearm identification or repair;

6/ To buy or sale authorized firearms.

**17. Firearm Registration System**

The Supervising Institution shall register and administer all firearms in the country by their serial number with information technology system.

www.chilot.me

## ክፍል አራት

## የጦር መሳሪያ አጠቃቀም ግዴታዎች

### ፲፰.ፍቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ መሰረት ፍቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

፩/የጦር መሳሪያውን በዚህ አዋጅ መሰረት ብቻ የመጠቀም፣

፪/የጦር መሳሪያውን ሲይዝ የፈቃድ ወረቀቱን አብሮ የመያዝ፣

፫/ፈቃድ ካገኘበት የጥይት መጠን በላይ አለመያዝ፣

፬/ የሚቻል እስከሆነ ድረስ የጦር መሳሪያው በግልፅ ሊታይ በማይችል ሁኔታ መያዝ፣

፭/ ፍቃዱን ካገኘ በኋላ ለፍቃድ ማግኘት መሰረት የሆኑ ሁኔታዎች እና መረጃዎች ላይ ማንኛውም ለውጥ ሲኖር ለተቆጣጣሪው ተቋም በ፲፭ ቀን ውስጥ ማሳወቅ፣

፮/ፍቃድ የወሰደበት ወይም በይዞታው የሚገኝ ጦር መሳሪያ ሲበላሽ፣ ሲጠፋ፤ ሲሰረቅ፣ ሲቀማ፣ የመለያ ምልክቱ ሲደበዝዝ ወይም በማንኛውም ምክንያት ከቁጥጥሩ ውጪ ሲሆን ለተቆጣጣሪው ተቋም በ፲፭ ቀን ውስጥ ማሳወቅ፣

፯/የፍቃዱ መጠቀሚያ ጊዜ ከማለቁ በፊት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የጦር መሳሪያውን ይዞ በአካል በመቅረብ እና ስለ ጦር መሳሪያው አጠቃቀም ሪፖርት በማቅረብ ማሳደስ፣

፰/ፍቃዱን ወይም የተፈቀደለትን የጦር መሳሪያ በማናቸውም መልኩ ለሌላ አሳልፎ ያለመስጠት፣ ያለማዋስ፣ እንዲጠቀምበት አለማድረግ እና በሌላ ሰው እጅ እንዳይገባ ማድረግ፣

፱/የጦር መሳሪያው ጥቅም ላይ በማይውልበት ወቅት በጥንቃቄ ተጠብቆ እንዲቀመጥ ማድረግ፣

፲/የጦር መሳሪያውን አገልግሎት ያልፈለገ ወይም ፈቃዱ የማይታደስለት እንደሆነ ለተቆጣጣሪው ተቋም የጦር መሳሪያውን መስጠት፣

## PART FOUR

## FIREARM UTILIZATION DUTIES

### 18. Duties of Licensed Person

Any person licensed in accordance with this proclamation shall:

1/use his firearm in accordance with this proclamation only;

2/hold the license certificate whenever carrying the firearm;

3/not carry more than authorized amount of bullets;

4/ as much as possible not carry the firearm openly;

5/ inform the Supervising Institution immediately whenever there is any change of information or condition after getting the license with regard to the basis for acquiring the license;

6/ inform the Supervising Institution with in 15 days whenever the firearm licensed or under his possession is lost, breaks down, stolen, snatched, the indentifying number fades up or is in any way out of his control;

7/ before the expiry of the license validity period appear in person with the firearm and renew the license by presenting report about its utilization;

8/not transfer the license or authorized firearm to others in any way, not lend it, not allow others to use it, make sure that it does not go into the hands of other person;

9/ keep the firearm safely while it is not in use;

10/handover the firearm to the Supervising Institution where one does not need the utility of the firearm or where the license is not to be renewed for him;

www.chilot.me

፲፩/የጦር መሳሪያ በሚያዝበት እና ጥቅም ላይ በሚያውልበት ወቅት በተቆጣጣሪው ተቋም የሚወጡ የጥንቃቄ ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ፣

ግዴታ አለበት።

**፲፱.የድርጅት ግዴታ**

የጦር መሳሪያ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት፡-

፩/የተፈቀደለትን የጦር መሳሪያ በዚህ አዋጅ መሰረት መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖ ለሚያገኘው ሰው ብቻ የማስያዝ፣

፪/የጦር መሳሪያው ጥቅም ላይ ሲውል ማን እንደያዘው የሚገልፅ እና የጦር መሳሪያውን የጥበቃ ሰራተኞች በመቀያየር የሚይዙት በሚሆንበት ጊዜ ርክክብ የሚፈፀምበት ቋሚ ስርአት መዘርጋትና መጠበቁን የማረጋገጥ፣

፫/የጦር መሳሪያውን በዚህ አዋጅ መሰረት ለተሰጠበት አላማ ብቻ የመጠቀም፣

፬/ፈቃድ ካገኘበት የጥይት መጠን በላይ ያለመያዝ፣

፭/ፍቃዱን ካገኘ በኋላ ለፍቃድ ማግኘት መሰረት የሆኑ ሁኔታዎች እና መረጃዎች ላይ ማንኛውም ለውጥ ሲኖር ለተቆጣጣሪው ተቋም ወዲያውኑ የማሳወቅ፣

፮/ፍቃድ የወሰደበት ወይም በይዞታው የሚገኝ ጦር መሳሪያ ሲበላሽ፣ ሲጠፋ፤ ሲሰረቅ፣ ሲቀማ፣ የመለያ ምልክቱ ሲደበዝዝ ወይም በማንኛውም ምክንያት ከቁጥጥሩ ውጪ ሲሆን ለተቆጣጣሪው ተቋም ወዲያውኑ የማሳወቅ፣

፯/የፍቃዱ መጠቀሚያ ጊዜ ከማለቁ በፊት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የጦር መሳሪያውን ይዞ በአካል በመቅረብ እና ስለ ጦር መሳሪያው አጠቃቀም ሪፖርት በማቅረብ የማሳደስ፣

፰/ፍቃዱን ወይም የተፈቀደለትን የጦር መሳሪያ ከሰራተኞቹ ውጪ ለሌላ ሰው በማናቸውም መልኩ አሳልፎ ያለመስጠት፣ ያለማዋስ፣ እንዲጠቀምበት አለማድረግ እና በሌላ ሰው እጅ እንዳይገባ ማድረግ፣

11/implement safety rules issued by the SupervisingInstitution while carrying and using firearm

**19. Duties of Organization**

An organization licensed to use firearm shall :

1/only permit persons who meet the requirements in this proclamation to hold the authorized firearm;

2/ lay down permanent handover system and ensure that this is maintained where guard members interchangeably bear it and shall indicate the person holding it when the firearm was utilized;

3/use the firearm in accordance with this proclamation for the intended purpose only;

4/not carry more than authorized amount of bullets;

5/ inform the Supervising Institution immediately whenever there is any change of information or condition after getting the license with regard to the basis for acquiring the license;

6/inform the Supervising Institution immediately whenever the firearm licensed or under its possession is lost, breaks down, stolen, snatched, the indentifying number fades up or is in any way out of its control;

7/before the expiry of the license validity period appear in person with the firearm and renew the license by presenting report about its utilization;

8/ not transfer away the license or authorized firearm to other person except its employees in any way, not lend it, not allow others to use it, make sure that it does not go into the hands of other person;

www.chilot.me

፱/የጦር መሳሪያው ጥቅም ላይ በማይውልበት ወቅት በጥንቃቄ ተጠብቆ እንዲቀመጥ የማድረግ፣

፲/ የጦር መሳሪያውን አገልግሎት ያልፈለገ ወይም ፈቃዱ የማይታደስለት እንደሆነ ለተቆጣጣሪ ተቋም የጦር መሳሪያውን መስጠት፣

፲፩/የጦር መሳሪያ በሚያዝበት እና ጥቅም ላይ በሚያውልበት ወቅት በፍቃድ ሰጪው ተቋም የሚወጡ የጥንቃቄ ደንቦችን ተግባራዊ የማድረግ፤

ግዴታ አለበት።

## ፳. በፍቃድ የተያዘ የጦር መሳሪያ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ ስለሚችልበት ሁኔታ

፩/የጦር መሳሪያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጦር መሳሪያ ለሌላ ሰው በማናቸውም መልኩ አሳልፎ መስጠት የለበትም።

፪/የጦር መሳሪያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጦር መሳሪያውን አገልግሎት ያልፈለገ እንደሆነ ለተቆጣጣሪ ተቋም ማስረከብ አለበት።

፫/ባለፍቃዱ የሞተ እንደሆነ በፍርድ ቤት የመውረስ መብት ያረጋገጠ መስፈርቱን የሚያሟላ ወራሽ የጦር መሳሪያው እንዲተላለፍለት ለመጠየቅ ይችላል።

፬/የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው እስኪፈፀም ድረስ የጦር መሳሪያው በእጁ የገባ ሰው በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪው ተቋም ማስረከብ አለበት።

## ክፍል አምስት
## ስለ ተቆጣጣሪ ተቋም

## ፳፩.ተቆጣጣሪ ተቋም ስልጣንና ተግባር

ተቆጣጣሪው ተቋም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/በስሩ ብሔራዊ የጦር መሳሪያ ቁጥጥር የስራ ክፍል አደራጅቶ ይህን አዋጅ ማስፈፀም፣ መቆጣጠር፣

9/keep the firearm safely while it is not in use;

10/ handover the firearm to the Supervising Institution where one does not need the utility of the firearm or where the license is not to be renewed for it;

11/implement safety rules issued by the Supervising Institution while carrying and using firearm.

## 20. Conditions where a Licensed Firearm may be Transferred to Another Person

1/a person with a firearm license shall not transfer the firearm to other person in any way;

2/where a licensee does not need the utility of the firearm, he shall handover the firearm to the Supervising Institution ;

3/where a license holder dies his heir who gets his right determined by court may request that the firearm be transferred to him, however if the heir could not be given the license, he may request the Supervising Institution to transfer it to another heir who meets the requirements;

4/ until the condition under sub article 3 of this Article are met, any person who holds the firearm shall, within 30 working days, handover the firearm to the Supervising Institution;

## PART FIVE
## SUPERVISING INSTITUTION

## 21. Power and Duties of the Supervising Institution

The Supervising Institution shall have the following powers and duties to enforce this Proclamation:

1/organize a national firearm control business unit under it and enforce and control the enforcement of this proclamation;

www.chilot.me

፪/በዚህ አዋጅ መሰረት የጦር መሳሪያ ለመጠቀም ፈቃድ መስጠትና ህገወጥ የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን መቆጣጠር፣

፫/ጉዳት አድራሽ ዕቃዎች ወደ ሀገር ማስገባት፣ ማምረት፣ ማዘዋወር፣ ማከማቸት፣ መሸጥ፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና ፈቃድ በሚወጣ ደንብ መሰረት መስጠት፣ መቆጣጠር፣

፬/ፈቃድ የሰጠበት ቅድመ ሁኔታ ተለውጧል ብሎ ሲያምን የሰጠውን ፈቃድ ማገድ፣ መሰረዝ፣

፭/ለህዝብ ሰላምና ደህንነት አስጊ ሆኖ የተገኘን ማንኛውንም ፍቃድ ያለውንም ሆነ ህገወጥ የጦር መሳሪያ የታጠቀን ሰው የማስፈታትና የመውረስ፣

፮/በህገወጥ መንገድ የተያዘን የጦር መሳሪያ በጥናት በመለየትና ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበርና በመተማመን ወደ ህጋዊ ስርአት ማስገባት ወይም ህገወጥ የጦር መሳሪያን ማስፈታት፣ ማስወገድና መውረስ፣

፯/በፍርድ ቤት ትእዛዝ በመንግስት እንዲወረስ ውሳኔ የተሰጠበትን፣ ፈቃድ የሌለውን፣ ባለቤቱ ያልታወቀ ወይም አገልግሎት ሊሰጥ የማይችልን የጦር መሳሪያ መውረስ፣ መወገድ ያለባቸውን ማስወገድና ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉትን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

፰/በዚህ አዋጅ መሰረት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የጦር መሳሪያዎችን ከውጪ ሀገር የማስገባት፣ ከሀገር የማስወጣት፣ የመያዝ፣ በጥንቃቄ የማከማቸት፣ የማዘዋወር፣ የማስተላለፍ፣ ከሃገር ውስጥ የመግዛት፣ የመሸጥ፣ ስለአጠቃቀም የማሰልጠን፣ የመጠገንና የማስወገድ፣ ተግባራትን ማከናወን፣ ወይም አስፈላጊነቱን በአመነ ጊዜ በተመረጠ አግባብነት ባለው መንግስታዊ ተቋም አማካኝነት እንዲከናወን ፈቃድ መስጠት፣

፱/የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚመለከቱ ጥናቶችን ማድረግ፣

2/give license to use firearm in accordance with this proclamation and control illegal use of firearm;

3/give professional competence certificate and control import, production, traffic, storage and sale of harm inflicting materials in accordance with Regulation to be issued;

4/suspend or revoke the license it gave when it believes the precondition under which the license given is changed;

5/disarm and confiscate licensed or illegal firearm which is found to be threat to public peace and security;

6/study and identify firearms carried illegally and bring them to e illegal legitimate scheme in cooperation and with the consensus of the society or disarm, dispose and confiscat firearm;

7/confiscate firearms determined by court order to be confiscated by the government, which do not have license, whose owner could not be determined or which could not render service; dispose firearm which needs to be disposed and make use of those which could be utilized;

8/Import, export, possess, safely store, traffic, transfer, buy locally, sale, train on how to use, repair and dispose of firearms in accordance with this proclamation or provide a permit for the appropriate government institution when it determines it necessary, to perform those activities

9/conduct researches related to firearm administration control;

www.chilot.me

፲/የጦር መሳሪያን ጎጂነት እና ህጋዊ አጠቃቀም በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራትን ማከናወን፣

፲፩/የጦር መሳሪያን በተመለከተ አለም አቀፍ ትብብር ማድረግ፣

፲፪/በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወሩ ወይም ጥቅም ላይ ሲውሉ የተያዙ የጦር መሣሪያዎች በተያዙበት መስተዳድር ወይም ከዚያ ከፍ ባለ አደረጃጀት ጥቅም ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ ወይም ወደ ተቆጣጣሪው ተቋም ተልከው ገቢ ስለሚደረጉበት ሁኔታ ሥርዓት ይዘረጋል፣

፲፫/ከጦር መሳሪያ አያያዝ፣ አጠቃቀምና መሰል ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርአት ይዘረጋል፣፡

፲፬/በሕጋዊ መንገድ የጦር መሣሪያ የታጠቀ ሰው የታጠቀውን የጦር መሣሪያ መሸጥ በፈለገ ጊዜ፣ የጦር መሣሪያ ትጥቅ ጥያቄ አቅርቦ መስፈርቱን ለአሟላ ሰው ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ በሽያጭ እንዲተላለፍ ያደርጋል፣የአሰራር ሥርዓትም ይዘረጋል፣

፲፭/በወንጀል ህጉ አንቀፅ ፬፻፹፩ ላይ የተመለከተው እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ ላይ የተመለከተው ሕገ-ወጥ ተግባር የተፈጸመው ተሽካርካሪ ወይም እንስሳትን በመጠቀም ከሆነ፣ ለዚህ ተግባር መፈፀሚያነት የዋለው ተሽከርካሪ ወይም እንስሳት ውርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል።

፲፮/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፲፭ ላይ የተደነገገው ቢኖርም ወንጀሉ የተፈጸመው ህዝብ በተሳፈረበት የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ላይ ሆኖ የተሽከርካሪው ባለቤት ስለድርጊቱ እንደሚያውቅ ካልተረጋገጠበት ወይም ስለድርጊቱ አውቆ አስፈላጊውን እርምጃ ስለመውሰዱ ማረጋገጥ ከተቻለ ወይም በተሽከርካሪው ላይ ባእድ አካል

10/conduct activities that could raise the awareness of the society about legal use and harmful nature of firearm;

11/conduct international cooperation in relation to firearm, serve as competent authority;

12/establish a mechanism to put into use by the local or higher level administrations where firearms were transported or used illegally;

13/establish a submission and processing system to complaints involving the possession, use of firearm and related issues;

14/establish a system, upon determining all requirements are met, to process the sale of a firearm when an individual who is legally permitted to possess a firearm submits a request,a system shall be set up;

15/if the crime indicated in the Criminal Code Article 481 and in the sub article 3 of this part of the Proclamation is committed using a vehicle or animals, the vehicle or animals employed to conduct the crime shall be confiscated and transferred into government ownership;

16/notwithstanding sub article 15, if the crime is committed in a public transport vehicle and if the owner is determined not to have known about the crime, or if it is determined he/she has taken necessary measures upon being made aware of the crime and unless a special compartment was discovered within the vehicle to hide and store the

www.chilot.me

ተሰርቶ በዚያው ውስጥ ተደብቆ ካልተገኘ በስተቀር የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪው አይወረስም፡፡

**፳፪.ወንጀል ተጠያቂነት**

፩/በጦር መሳሪያ መነገድ ወንጀል በሚመለከት የወንጀል ህግ አንቀፅ ፬፻፹፩ የተጠበቀ ነው፣

፪/ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ክልከላ እና ግዴታ በመተላለፍ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ፣ የጦር ሜዳ መነፅር፣ በጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛውም አይነት መነፅር ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምፅ ለማስወገድ የሚያገለግል መሳሪያ ወደ ሀገር ያስገባ፣ ከሀገር ያስወጣ፣ ያስቀመጠ፣ የተገለገለ፣ ያሣየ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያጓጓዘ፣ ያመረተ፣ ያሰለጠነ፣ የጠገነ ወይም ያስወገደ፣፣በማናቸውም መንገድ ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ ከአንድ አመት እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ እስከ አስር ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣፣

፫/በዚህ አንቀፅ ንኡሰ አንቀፅ ፪ የተፈጸመው ወንጀል ብዛት ባለው የጦር መሣሪያ ሲሆን ቅጣቱ ከስምንት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከመቶ ሺ. እስከ ሁለት መቶ ሺ. ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

፬/በህጋዊ መንገድ የታጠቀውን የጦር መሳሪያ ተቆጣጣሪው ተቋም ሳይፈቅድ የሸጠ ማንኛውም ሰው ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፣

፭/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፬/ በተመለከተው አግባብ የጦር መሳሪያው የተሸጠው ለአሸባሪ ወይም ለሌላ ህገ-ወጥ ቡድን ከሆነ ከአንድ አመት እስከ ሶስት አመት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት አመት በሚደርስ ቀላል እሰራት ይቀጣል፣

፮/በህጋዊ መንገድ የታጠቀውን የጦር መሳሪያ

firearm, the vehicle shall not be confiscated;

**22. Criminal Liability**

1/Article 481of the Criminal Code dealing with arms trafficking shall remain in effect;

2/Any person who in violation of the prohibition and duty indicated under this proclamation without having valid license Import, export, put, use, exhibit, broker, sell, buy, put in circulation , produce, Train, repair; dispose, transfer in any way or carry, firearm, military binoculars; any kind of goggles or sound muzzling instrument which may be fitted on firearm; shall be punished with simple imprisonment of one year to three years and fine from five thousand birr up to ten thousand birr;

3/If the crime indicated under sub article 2 of this article is committed with bulk firearm,he/she shall be punished with rigorous imprisonment of between eight to twenty(8 -20) years and a fine between 100,000 – 200,000(hundred thousand to two hundred thousand) Birr;

4/Anyone who sells his/her legally licensed firearm without the permit by the Supervising Institution, shall be punished with a simple imprisonment of not more than one year;

5/under sub article 4 of this Article, if the firearm is sold to a terrorist or other illegal group, he/she shall be punished with a simple imprisonment of between 1 – 3(one to three) years or, based on the circumstances of the offence, up to 5(five) years.

6/Anyone who mortgages or transfers to a third party his/her legally licensed firearm will be punished with

በማስያዣነት የተጠቀመ ወይም በትውስት ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፣

፯/በአምራቹ ወይም በተቆጣጣሪ ተቋም የተሰጠ የጦር መሳሪያን የውግ ቁጥርን በሙሉ ወይም በከፊል የቀየረ፣ ያጠፋ ወይም በማናቸውም አይነት ሁኔታ ተለይተው እንዳይታወቁ ያደረገ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር እስከ ሁለት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፣

፰/የጦር መሳሪያን ወይም የጦር መሳሪያን የተመለከተ አገልግሎት ያስተዋወቀ ማንኛውም ሰው ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፣

፱/ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ክልከላ እና ግዴታ በመተላለፍ ጉዳት አድራሽ እቃዎችን በብዛት ያስቀመጠ፣ የተቀበለ፣ ያከማቸ፣ ያጓጓዘ፣ ያዘዋወረ፣ የደበቀ፣ የተገለገለ፣ ያሳየ፣ የያዘ፣ የገዛ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ የደለለ፣ በማናቸውም መንገድ ያስተላለፈ፣ ወደ ሀገር ያስገባ፣ ከሀገር ያስወጣ፣ ያመረተ፣ ያስወገደ የጠገነ እንደሆነ ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከአንድ ሺህ እስከ አምስት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

፲/በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፭ የተመለከተውን የመተባበር ግዴታ የጣሰ ማንኛውም ሰው እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል።

፲፩/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ እስከ ፰ የተመለከቱት ተግባራት የተፈጸሙት የህግ ሰውነት መብት በተሰጠው ሰው ከሆነ ከአምስት መቶ ሺህ ብር እስከ ሁለት ሚሊዮን ብር የሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፲፪/በወንጀል ህጉ አንቀፅ ፬፻፹፩ ላይ የተመለከተው እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ ላይ የተመለከተው ተግባር የተፈጸመው ተሽካርካሪ በመጠቀም ከሆነ፣ ለዚህ ተግባር መፈፀሚያነት የዋለው ተሽከርካሪ

a simple imprisonment of not more than one year;

7/.Anyone who alter in whole or in part, destroy or make unrecognizable in any other way the serial number of a firearm given by the manufacturer or supervising institution shall be punished with simple imprisonment of six month to two years;

8/Anyone who Advertise firearm or service related with firearm shall be punished with simple imprisonment of not exceeding one year.

9/Any person who in violation of the prohibition and duty indicated under this proclamation put, receive, store, Transport, put in Circulation, Hide, use, exhibit, carry, buy, sell, offer to sell, broker, in any way transfer, import, Export, produce, dispose or repair, of harm inflicting materials in bulk shall be punished with simple imprisonment not exceeding one year and fine from one thousand birr up to five thousand birr

10/Any person who violates duty of cooperation indicated under article 25 of this proclamation shall be punished with simple imprisonment of not exceeding three years.

11/ If offences indicated from sub Article 2 to 8 of this Article are committed by an entity given a legal person status, the punishment shall be between 500,000 – 1,000,000 birr( five hundred thousand to two million) birr

12/when an act indicated in article 481 of the criminal code and sub article 3 of this article is committed Using Vehicle, the vehicle which is used to commit such act shall be Confiscated by and delivered to the

www.chilot.me

በጉምሩክ ኮሚሽን አስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት ውርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፫·የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በነበሩ ህጎችና አሰራሮች ተመዝግበው ወይም ፍቃድ ተሰጥቷቸው የነበሩ የጦር መሳሪያ የመያዝና የመጠቀም ፍቃዶች በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ በአካል ቀርበው ፍቃድ መጠየቅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው በተቆጣጣሪ ተቋሙ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፣፣

፪/ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በነበሩ ህጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፍቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ መጠየቅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው በተቆጣጣሪ ተቋሙ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፣

፫/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና ፪ መሰረት ፈቃድ ያላገኙ ሰዎች የያዙትን የጦር መሳሪያ ለተቆጣጣሪው ተቋም ማስረከብ አለባቸው፣

### ፳፬. የመተባበር ግዴታ

፩/ማንኛውም ሰው የተቆጣጣሪው ተቋም በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ሃላፊነቶችን ለመወጣት የሚጠየቀውን መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፣

፪/ማንኛውም ሰው ተቆጣጣሪ ተቋሙ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወስደውን እርምጃ የማክበርና ለዚሁ የመተባበር ግዴታ አለበት።

government by the Administrative decision of Customs Commission.

## PART SIX
## MISCELANEOUS PROVISIONS

### 23. Transitory Provisions

1/Firearm possession and use license or registration given in accordance with laws and practices prevailing before the coming into force of this proclamation, shall take a new license within two years from the supervising institution per the announced schedule and by meeting all requirements indicated under this proclamation.

2/Persons carrying or using firearm without license or registration based on laws and practices prevailing before the coming into force of this proclamation, shall take license from the supervising institution within one year by fulfilling requirements indicated under this proclamation as per the schedule that it announces;

3/Persons who do not get license in accordance with sub article (1) and (2) of this Article shall handover their firearm to the Supervising Institution;

### Duty to Cooperate

1/Any person shall be responsible to provide information requested by the supervising institution to undertake its duties indicated under this Proclamation;

2/Any person shall have the duty to respect and cooperate with measures taken by the Supervising Institution in order to enforce this Proclamation.

www.chilot.me

**፳፬.ለህግ አስከባሪ አካላት የጦር መሳሪያ አያያዝ ፣አይነትና ብዛት**

የዚህ አዋጅ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በፌዴራልና በክልል የሚገኙ የህግ አስከባሪ አካላት የጦር መሳርያ አያያዝ፣ አይነት እና ብዛት በሚመመለከት ተልእኮአቸውንና ሌሎች ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፳፭.ስለ መከላከያ ሰራዊት እና ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት**

የመከላከያ ሰራዊት እና ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣

፩/የሚታጠቁትን የጦር መሳሪያ አይነት፣ ብዛት እና የአጠቃቀሙንም ሁኔታ በራሳቸው ይወስናሉ፣

፪/ከተቆጣጣሪው ተቋም ጋር በጋራ አስፈላጊ ሆነው በሚያገኟቸው ጉዳዮች ላይ ተባብረው ይሰራሉ፡፡

**፳፮.ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣፣

፪/ተቆጣጣሪ ተቋሙ ይህን አዋጅና፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣ ደንብን ለማስፈፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

**፳፯.የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች**

፩/የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፪፻፳፱/፲፱፻፶፪ በዚህ አዋጅ ተሽሯዋል፡፡

፪/የወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፰፻፰ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፫/ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**24. Firearm utilization, Type and Amount to be Authorized for Law Enforcement Bodies**

The type and Amount of Firearm that the Federal and Regional law Enforcement Bodies can bear shall be determined based on their mission and other situations by regulation to be issued by the Council of Ministers;

**25. Defense Force and National information and security Service**

Defense Forceand National information and security Service shall:

1/determine by themselves the type, amount and condition of use of firearm that they are armed;

2/work in cooperation with the Supervising Institution on issues which they mutually find necessary.

**26. Power to Issue Regulation and Directive**

1/The Council of Ministers may issue Regulation necessary to enforce this Proclamation.

2/The Supervising Institute shall issue directive necessary for the enforcement of this Proclamation and regulations issued in accordance with this proclamation.

**27. Repealed and Inapplicable Laws**

1/Legal notice 229/1960, is hereby repealed;

2/Article 808 of the Criminal Code is here by repealed;

3/No law, regulation, directive or practice in so far as it is inconsistent with this proclamation, shall be applicable with respect to matters covered by this proclamation.

www.chilot.me

**፳፱. <u>አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

**28. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into effect as of 8th day of January 2020 as ratified by the House the Peoples Representatives.

Done at Addis Ababa, this 25th day of March, 2020.

**SAHILEWORK ZEWUDE**

**PRESIDENT OFTHE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me